## የሕዝብ ተቀባይነትን ለመግዛት እነ ልደቱ አያሌው እንደ ብርቱካን ሁሉ ከርቸሌ በመዉረድ ዕድላቸዉን መሞከር ሳያስፈልጋቸዉ አይቀርም፤

# መታሰር ብቻዉን መሠረታዊ የሕዝብ ድጋፍ አያመጣም

በሕሊና በለጠ Jan 18, 2008

የዚህ ጽሁፍ ዋና አላማ ወያኔ በእስር ቤት ሳቢያ ወያኔ በኢትዮጲያ ሕዝብና ታሪክ ላይ ፈጸመዉን በደልና ተግባር ለመግለጽ ነው፡፡ ባለፉት ስርዐት እንደተለመደዉ ሁሉ በተለያየ ምክንያት የሕዝቡን ትግል ነፃነትና ለማፈን እስር ቤቶች እንደ ትልቅ መሣሪያ ሆነዉ ሲያገለግሉ መቆየታቸዉ ይታወሳል፡፡ በወያኔ ስርዐት ግን ከሁሉም በተለየና በረቀቀ መልክ እስርቤቱንና እስረኞቹን ለፖለቲካዉ ማስጠበቂያ በማድረግ ሲጠቀምባቸዉ ቆይቷል፡፡ ዛሬ ወያኔ በኢትዮጲያ ሰዎች የሚታሰሩት በወንጀ ወይም በፍታብሔር መተላለፍ ብቻ እንጂ የፖለቲካ እስረኞች እንደሌሉት ደጋግሞ ገልጿል፡፡ የእስር ቤቱ አስተዳደርም ቢሆን ላገሪቱ የተዘጋጀዉን የወንጀለኛና የፍታብሔር ሕግ ለማስፈፀምና ለሕዝብ ለመቆም ሳይሆን የመንግስትን ፖለቲካዊ ስነ ምግባር ብቻ የሚያስጠብቅ በመሆኑ እስር ቤቶች እና ፍረድ ቤቶች ባላቸዉ ተያያዥነት ከፍተኛ የሕዝብ በደል የሚፈጸምባቸዉ ቲያትር ቤቶች ሆነዋል፡፡ በመሆኑም ወደ እስር ቤት የሚወርዱ ሰዎች ያስተሳሰር ቅደም ተከተል ወይም ቡድን ተበጅቶላቸዋል፣ ይኸዉም በተለያየ ወንጀል የገቡ ሰዎችን በተለያየ ጥቅማ ጥቅም በመግዛት እስረኞቹ ለመንግሥት እንዲሰሩ እየተደረገ ነው፡፡ በተለይም በእስር የሚገኙትን የፖለቲካ ሰዎች ወይም መንግስት ጎጂ የሚላቸዉን አካሎችን እንዲከታተሉና መረጃ እንዲያቀብሉ በማድረግ እስረኛዉ በአንድነት እንዳይቆምና ለመብቱ እንዳይከራከር መሰሪ አካሄድ እየተከናወነበት ይገኛል፡፡ በዚህም አካሄድ የእስር ቤቱ አስተዳደር የፖለቲካ ድርሻ ተሰጥቶት በእስረኛው ላይ በትእዛዝ የሚያደርሰዉ ደባና በደል ከፍተኛ ነዉ ፡፡ ፍርድ ቤት ልክ እንደ እስር ቤት ሁሉ ወያኔ የሚገለገልበት፤ትልቅ መዋቅር ነው ፣ ፍረድ ቤቱ በሚያዘጋጀዉ የሀሰት ማስረጃና ምስክር ሰዎች ለእስር ቤት ይጣላሉ፣ ሲያስፈልግም መንግስት በሚሰጠዉ ትእዛዝ መሠረት ረጅም ቀጠሮ በመስጠትና እስሩን በማራዘም የመንግስትን ትልቁን ሚና በመጫወት ይተባበራል ይህም በምርጫ 97ቱ እስረኞች ላይ በተግባርወ የታየና የተረጋገጠ ነዉ፡፡ በተለይ ወቅታዊ የሕዝብ ጥያቄዎችን ያነገቡ ቡድኖችንና ሰልፎችን ለማፈንና ለመቅጨት እስር ቤት በመወርወር የሕዝቡን ፍላጎት አውርዶ ለሕዝቡን ሌላ አጀንዳ እያዘጋጅ የራሱን የፖለቲካ ሕጋዊነት ማረጋገጫ አድርጎታል፡፡ ከሁሉም በላይ የሚገርመዉ ታራሚ የሚለዉ ስም ለሁሉም እስረኞች የተሰጠ በመሆኑ ነዉ፡፡ ለመሆኑ አንድ እስረኛ እነሱ ባዘጋጁትም ወጠመድ ቢሆን ተፈርዶበት ወንጀሉ እስካልተረጋገጠ ድረስ የትኛዉን ስህተቱን ለማረም ነዉ ታ ራሚ የሚለዉ ስም የሚሰጠዉ፣ ይህ የሚያስረዳዉ ግን በእስር ቤት ዉስጥ የሚካሂደዉን ሰቆቃና ኢ -ሰባዊነት በስም ለማቃለል የተደረገ መሸፈኛ መሆኑን ነዉ፡፡ በዚች መታሰር አገራዊ ግዴታ በሆነባት አገር ኢትዮጲያ መንግሥት ባዘጋጀዉ የቅጣት ወጥመድ ተራዉን የሚጠብቀዉ የሕዝብ ክፍል ለፖለቲካ እስረኞች ያለዉ አመለካከትና ድጋፍ ከፍተኛ ነዉ፡፡ ሆኖም የኢትዮጲያ ሕዝቡ ሊያስተዉልና ሊያጤነዉ እንዲሁም ካለፈዉ ልምድ ሊማር የሚገባዉ ጉዳይ አለ፣ ወያኔ በተለያየ መንገድ ሕዝብን እንደሚያስርና የሕዝብንም ትግል እንዴት እንደሚያኮላሽ በተግባር ያየነዉ ስለሆነ ጠንቀቅ ማለትን የሚጠይቅ ሆኗል፡፡ በዚህም ሀሳብ ዉስጥ በጥልቀት ገብቶ መዘርዘር አያስፈልግም፤ ምክንያቱም ልክ እንደ ትላንቱ ሁሉ ነገ እዉነቱ አፍጥጦ መዉጣቱ አይቀሬ ነዉና ነዉ፡፡ እዉነተኛ የፖለቲካ ተዋናዊያኖችን ከቲያትረኞች ለይቶ ማወቅ የሕዝቡ ግዴታ ነዉ፡፡ ሰዉ በአንድ አይነት ሁኔታና ስልት ከአንዴ በላይ አይታለልም ሊታለልም አይገባም፡፡

በምርጫ 97 ሳቢያ ከተከሰተዉ እስር በኋላ አንድም ቀን ወያኔን የሚነቅፍ ሀሳብ በመድረቅ ላይ ያላነሱ ሰዎች ድንገት በቅጽፈት ያዉም በአሉባልታ እንዴት እስር ቤት ሊገቡ ይችላሉ፡፡ አሁን እንኳ የተዘጋጀዉ ሰበብ ነባራዊ ሁኔታን ያላገናዘበ በመሆኑ የሚሠራም አይመስልም ምክንያቱም

ወዘሪት ብርቱካን ለምን ታሰረች ሲባል
ከእስር ስንወጣ የፈረምነዉ በግድ ነዉ
ስላች ነዉ የሚል መልስ ነዉ የተሰጠዉ፡፡

ለመሆኑ
ይህ የታሰረችበት ጉዳይ ሕዝቡ ለተዋደቀለት ዋና ትግልና ጥያቄ
የሚ ያበረክተዉ አስተዋጾ ምንድን ነዉ ?

ባይሆን ለማምታታትም እንዲያመች እንኳን ታፍነዉ ከተያዙት የሕዝብ ጥያቄዎች ጥቂቶቹን አንግበዉ ወደ እስር መግባት ሕዝቡን ለማሳሳት ለታቀደዉ እቅድ ጥቂት መንገድ ይወስድ ነበር፡፡ ዛሬ የኢትዮጲያ ሕዝብ የሚፈልገዉ የመሠረታዊ ለዉጥ ሊያመጡ ከሚችሉ ዋና ዋና ጥያቄዎች ጥቂቶቹን እንኳን ይዞ የሚወጣና ለዘመናት ያለዉን ጭቆናና ግፍ በመጠኑም ቢሆን በማላላት ለልጆቹ የተሻለ ነገር ማቆየትን ነዉ፡፡

እንዳለፈዉ ሁሉ በተደረገዉ የፕሮፓጋንዳ ሙስና የሰዎችን ጀግንነት እንደ አሻንጉሊት ሰርቶ ማቆም ቢቻልም ዛሬ የኢትዮጲያ ሕዝብ ነቅቷል፡፡ ጠንካራ የፖለቲካ ሰዉ ለመባል ከኢትዮጲያ ሕዝብ ጠላት ስር ወጥቶ የሕዝብ ጥያቄን ማንገብና መ ጮህ ይጠይቃል። ጾታንም ቢሆን እንደ መጠቀምያ መሣሪያ መገልገል ከህሊና ተጠያቂነት አያስመልጥም ምክንያቱም ተናጋሪዋ እንዳሉት እጠቅሳለሁ “**It is not a matter of gender, it is a matter of agenda”** ስለዚህ

የኢትዮጲያ ሕዝብ ስለ ግለሰቦች ስምና ተራ ዝና የሚሠራ ተራ ቡድን ሳይሆን
እዉነተኛ የሕዝብን ጥያቄዎች ይዞ የሚታገል ሀቀኛ አመራር አካል ይፈልጋል፡፡
ወያኔ በሚያዘጋጀዉ ቲያትር መሪዎቻችንን ሊፈጥርልን አይችልም፡፡

ሕዝቡ የራሱን መሪ እራሱ መርጦ እዉነተኛ እኩልነትና የኑሮ መሻሻል የሚከሰትበትን ግዜና መድረክ ለመፍጠር መጣር አለበት፣ ዲሞክራሲዊ ነኝ የሚለዉ ወያኔ በጀርባ ከሚያከናዉነዉ ፀረ ሕዝብ ተግባር በተጨማሪ ሕዝቡ በመ ናገሩ በመጻፉና በመወያቱ የሚከፈልዉ ዋጋ እስርና ስቃይ ሆኑአል፡፡ ወያኔ ባሳለፈዉ የረጅም ግዜ አገዛዝ የተነሳ ሕዝቡ በራሱ የየሚተዳደርበትን ሁኔታ ዎች ዕዉን ለማድረግ የሚ ያስችለዉን ዘርፎች ሊያመቻች በተገባ ነበር፣ ነገር ግን ይህን ነፃነት በችሮታ ሊሰጠን ስለማይቻለዉ ሕዝቡ ጠንክሮና አምርሮ ሊታገል ይገባል፡፡ የሕዝብ መንግስት ከሕዝብ ይወጣል እንጂ እንደ ስጦታ ዕቃ ሊበረከትለት አይችልም፡፡ ወያኔ ሕዝቡን ልክ እንደ አሜባ በየቀኑ እየከፋፈል ወደፊት ከመሄድ ይልቅ በመከላከል ላይ ወይንም ባለበት እንዲቆም በማድረግ ትግሉ በይቀኑ በሚገጥመዉ አደጋ እንደገና ወደኋላ እየተመለሰ በመዝቀጥ ላይ ነዉ፡፡

ሌላዉ በጣም የሚያስገርመዉ ነገር የዲያስፖራዉ ጉዳይ ነዉ ፣ ዛሬ የኢትዮጲያ ሕብረተሰብ በዲያስፖራ ቁጥሩ ቀላል ግም ት የማይሰጠዉ ነዉ፣ ይህን የዲያስፖራ ቡድን ጥቂት ሰዎች ሲያወናብዱትና ተጨባጭ ሥራ እንዳይሠራ ሲያሰናክሉት ይታያል፡፡ በተለይ በሰልፍ በስብሰባና በገንዘብ መዋጮ ሰበብ ዲያስፖራዉ ምን ያህል እንደተቦረቦረና ተጠቃሚዎቹ ደግሞ እነዛ ደሃ ወገኖቹ ሳይሆን ጥቂት ግለሰቦች መሆናቸዉ የአደባባይ ሚስጥር ነዉ፡፡ በተለይም አርቲስቶችና የመድረቅ ሰዎች በትግሉ ስም የሚያከናውኑት ኢ -ወገናዊ ተግባር የሚያሳዝን ነዉ፡፡ ይህም ሲባል ሁሉንም በአንድ ለይ ለመጠቅለል ሳሆን ይህንን ተግባር ሥራ አድርገዉ የያዙትን ሰዎች ስም ዝርዝር መጻፍ ይቻላል፡፡ ወያኔና ሌሎች አካሎችም ዲያስፖራዉን ለመከፋፈልና አመርቂ የፖለቲካ ዉጤት እንዳይመዘገብ ለማድረግ የሚያፈሱት ገንዘብ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት ፖለቲካዉ ዉዥንብር ዉስጥ ገብቶ የማያፈራ የፓል ቶክ (**Pal Talk)** እንቶ ፈንቶ ብቻ ሆኖ ቀርቷል፡፡ እዉነት የአገር ወገን ጉዳይ ያንገበግኛል የሚል ወገን ሁሉ ከዚህ ዉዥንብር በመዉጣት ሆኔታዎችን አጢኖና አስተዉሎ በመለየት አገር ቤት ያለዉን ችግር ሊፈታ የሚያስችል የተግባር እንቅስቃሴ በማድረግ ወገናዊ ባላደራነቱን ሊወጣ ይገባል

በሚቀጥለዉ የፖለቲካ አጀንዳዎች አለመስተካከልና ቅደም ተከተላቸዉ በሚለዉ በተለይም ሕብረት ያስፈልጋል በሚባለዉ ሀሳብ ላይ ለማተት እሞክራለሁ